የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

## በብሔራዊ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ላይ የሚካሄድ የግብዐት ማሰባሰብና ምክክር የማስጀመሪያ መርሀ-ግብር አጭር መግለጫ

(Synopsis)

የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን መተግበር ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና ለህግ የበላይነት መረጋገጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ ነው። በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ቁርሾዎች አግባብነት ባለው፣ ሁለንተናዊ፣ የተቀናጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ ሳይፈቱ ሲንከባለሉ የመጡ ከመሆኑ አንጻር - በደሎች እንዲሽሩ፣ ቁርሾዎች እንዲጠገኑ እና ወደ ዲሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር እንዲሳካ ከተፈለገ፤ እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ እንዲቻል የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ሀገራዊ አውዱ ያመላክታል።

በሀገራችን ያለፉትን መጠነ ሰፊ እና ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ በደሎች፣ ዝንፈቶች፣ ቁርሾዎች እና ሌሎች ኢ-ፍትሀዊነቶችን - እውነትን፣ ፍትህን፣ ሰላምን እና እርቅን መሰረት ባደረገ ሁሉን-ዐቀፍ የሽግግር ፍትህ ስልት እንዲፈቱ ማድረግ - ለሰላም ግንባታ፣ ለዘላቂ የሰው ልጆች ልማት፣ ለማኅበራዊ ትስስር እና ለአገር ግንባታው አይተኬ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል። ከዚህ አንጻር በተሟላና በተቀናጀ መልኩ የሚዘረጋ አሳታፊ፣ ተጎጂዎችን ማእከል ያደረገ፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን ያከበረ፣ እንዲሁም የሀገራችንን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድን መሰረት ያደረገ የሽግግር ፍትህ ሂደት መቀመር እና በግልፅ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲመራ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም በሀገራችን ከነበሩት ሙከራዎች ልምድና ትምህርትን በመውሰድ - ዓለምአቀፍ ተመክሮዎችንና ምክረ ሀሳቦችን ባካተተ መልኩ - የሽግግር ፍትህ ሀገራዊ ዐውዱን በጠበቀ መልኩ በምን አግባብ ሊመራ እና ሊተገበር ይገባል የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ - ለዚህ መነሻ የሚሆን የጥናት ሰነድ በዘርፉ ሰፊ እውቀት ባላቸው ምሁራን እና ባለሙያዎች እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ጥናቱን መሰረት በማድረግም የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ተለይተው ከባለድርሻ አካላት ግብአት ለመሰብሰብ ተጨማሪ ሰነድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ሰነዱ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን - በክፍል አንድ የሽግግር ፍትህን ታሪካዊ ዳራ እና ሀገራችን ካለችበት ሁኔታ አንጻር ያለውን አስፈላጊነት፣ በክፍል ሁለት በሀገራችን የሽግግር ፍትህን በተመለከተ ያሉትን አማራጮች እና ምክረ ሀሳቦች፣ በክፍል ሶስት ደግሞ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊመራባቸው የሚገቡ መሰረታዊ መርሆዎች እና የማስተባበር እና የአደረጃጀት አማራጮች ቀርበዋል።

በአጠቃላይ የረቂቅ የፖሊሲ ሰነዱ ዝግጅት በባለሙያዎች ታግዞ ህዝባዊ ተሳትፎን ባረጋገጠ መልኩ ማከናወን እንዲቻል - በርካታ የውይይት መድረኮችን በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ማካሄድ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ የፌዴራል መንግስት ተቋማት፣ የክልል መንግስታት ተቋማት፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሲቪል እና ፖለቲካ ማህበረሰቦች፣ የተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች፣ እና የድጋፍ ሰጪ እና የአጋር አህጉራዊና አለማቀፋዊ ድርጅቶች ርብርብና ተሳትፎ አስፈላጊነት እጅግ ከፍ ያለ ነው።

ከዚህ አንጻር እና በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል ተመሳሳይ የአላማ አንድነት እና አረዳድ መፍጠር ተገቢ በመሆኑ ይህ መድረክ እንዲዘጋጅ ሆኗል።

**የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን**